በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 217220

ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡ ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ፡- አልቀረቡም

ተጠሪ ፡ ሲ/ር ፈለጉሽ ዳርጌ፡- ተወካይ ሳሙኤል ዳርጌ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የሥራ ክርክር ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች መልስ ሰጪ ተጠሪ ደግሞ ይግባኝ ባይ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ መስከረም 27 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ በአመልካች ዩኒቨርሲቲ ክሊኒክ ክፍል ኃላፊ በመሆን እየሰራሁ እያለ በ2006 ዓ.ም ነጻ የትምህርት እድል አግኝቼ ተምሬ ከጨረስኩ በኋላ በ2009 ዓ.ም ወደ ሥራ ተመልስሼ አመልካችን ምደባ ስጠይቅ በሥነ-ምግብ የሥራ መደብ ላይ እንድሰራ በሰኔ 09 ቀን 2009 ዓ.ም የተጻፈ የምደባ ደብዳቤ ተሰጥቶኛል፡፡ ነገር ግን የተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክተር የሥራ መደቡ ስለሌለ ሊያሠራኝ እንደማይችል ሲገልጽልኝ ይህንኑ ለሰው ሀብት

አስተዳደር ክፍል ወዲያውኑ ያሳወኩ ቢሆንም በህዳር 03 ቀን 2012 ዓ.ም በተጻፈ የጥሪ ማስታወቂያ በሥራ ላይ ሳልተገኝሁበት ማስረጃ አቅርቢ ተብያለሁ፡፡ እኔም ሥራ መስራት ያልቻልኩት የሥራ ምደባ ስላልተሰጠኝ መሆኑን ብገልጽም ከታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ደመወዜ እንዳይከፈለኝ ታግዷል፡፡ በመሆኑም የሥራ ምደባ እንዲሰጠኝ እና ደመወዜ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በጥቅምት 13 ቀን 2013 ዓ.ም የተጻፈ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና አማራጭ መልስ ያቀረበ ሲሆን አንዱ የአመልካች መቃወሚያ ተጠሪ ምደባ አልተሰጠኝም በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ታይቶ በበላይ ኃላፊ የመጨረሻ ውሳኔ አልተሰጠበትም የሚል ሲሆን የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ መቃወሚያውን ተቀብሎ ተጠሪ ያቀረቡትን የምደባ ጥያቄ በብይን ውድቅ አድርጓል፡፡ አመልካች በአማራጭ በሰጠው መልስ ተጠሪ ምንም አይነት የሥራ ምደባ አልተሰጠኝም በማለት የገለጹት ሀሰት ነው፡፡ በሰኔ 09 ቀን 2009 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በሥነ-ምግብ የሥራ መደብ ላይ ተመድበዋል፡፡ ተጠሪ የሥራ መደቡ የለም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው በማስረጃ ያልተረጋገጠ ነው፡፡ ተጠሪ ሥራውን ያልሰሩት የሥራ መደቡ አይመጥነኝም በሚል እንጂ መደቡ ስለሌለ ወይም ሥራው ስለሌለ አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ሥራ ሳይሰሩ ደመወዝ ሊከፈላቸው ስለማይችል ደመወዝ እንዲከፈላቸው መጠየቅ አይችሉም በሚል ተከራክሯል፡፡

የአስተዳደር ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አመልካች ተጠሪ ለሶስት አመት ተከል በሥራ ገበታቸው ላይ አለመገኘታቸውን ገልጾ የሚከፈላቸውን ደመወዝ አግዷል፡፡ የተጠሪ ስም በአመልካች መስሪያ ቤት የሰአት መቆጣጠሪያ ላይ የለም፡፡ አመልካች ሠራተኛን የመቆጣጠር ግዴታውን ሳይወጣ በደፈናው ተጠሪ ሥራ ላይ አልተገኙም በሚል የሚያቀርበው ክርክር ተቀባነት የለውም፡፡ አመልካች ተጠሪን በሥራ ላይ አልተገኙም ካለ ስማቸውን የሰአት መቆጣጠሪያ ላይ አስገብቶ ሥራ ላይ እንዳልተገኙ የሚገልጽ ምልክት በማድረግ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ነበረበት፡፡ በአጠቃላይ አመልካች ተጠሪ በሥራ ላይ አልተገኙም ብሎ ቢከራከርም አለመኖራቸውን በማስረጃ አስደግፎ ያላስረዳ በመሆኑ ከታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ተገቢውን ተቀናሽ በማድረግ ለተጠሪ ደመወዝ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ቅሬታው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

አመልካች በህዳር 27 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር ቅሬታ ያቀረበው በአስተዳደር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መጽናቱን በመቃወም ተፈጽሟል የሚለውን የህግ ስህተት ለማሳረም ነው፡፡ የቅሬታው ይዘት ተጠሪ ምደባ አልተሰጠኝም በሚል ያቀረቡት ቅሬታ ለበላይ ሀላፊ ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ ያልተሰጠበት ነው በሚል በብይን ውድቅ ከተደረገ በኋላ ይህንን ብይን በሚቃረን መልኩ ተጠሪ ደመወዝ እንዲከፈላቸው መወሰኑ፤ ተጠሪ ሥራ መስራት አለመስራታቸው አከራካሪ ባልሆነበት አመልካች ተጠሪ ሥራ ላለመስራታቸው ማስረጃ አላቀረበም መባሉ እና የተጠሪ የሥራ ስንብት ህጋዊ ሆኖ እያለ ደመወዝ ይከፈላቸው መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰበር አጣሪ ችሎት የአመልካችን የሰበር ቅሬታ መርምሮ ተጠሪ ከትምህርት ከተመለሱ በኋላ በሰኔ 09 ቀን 2009 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የሥራ ምደባ ተሰጥቷቸው አለመሥራታቸው ባልተካደበት እና በተመደቡበት የሥራ መደብ ላይ እንዳይሰሩ ስለመደረጉ ማስረጃ ባልቀረበበት ከሥራ መታገዳቸው አግባብ አይደለም በማለት ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈላቸው የመወሰኑን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 1064/2010 ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ተጠሪም በጥር 17 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ ከስር ጀምሮ የነበረው ክርክር የደመወዝ መታገድን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ከሥራ ስለመሰናበቱ ያነሳው ክርክር ሳይኖር ስንብቱ ህጋዊ ነው የሚል ክርክር ማቅረቡ ተገቢ አይደለም፡፡ የማስተርስ ትምህርት ጨርሼ ስመለስ አመልካች የምደባ ደብዳቤ የሰጠኝ ቢሆንም በተማሪዎች አገልግሎት ስር የሥነ-ምግብ የሥራ መደብ አለመኖሩን በዳይሬክቶሬቱ ተገልጾልኛል፡፡ አሁንም ድረስ ይህ የሥራ መደብ የለም፡፡ አመልካች ምደባ እንዲሰጠኝ በተደጋጋሚ የጻፍኩት ደብዳቤ በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ በማስረጃነት ቀርቧል፡፡ አመልካች ምደባን በተመለከተ ገና በመስሪያቤቱ ኃላፊ ውሳኔ የሚሰጥበት ነው በሚል የተከራከረ በመሆኑ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ለተጠሪ ምደባ ተሰጥቷት ነበር ወይስ አልነበረም? የሚል ጭብጥ በመያዝ የሚያጣራበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም በስር አስተዳደር ፍርድ ቤት እና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም በየካቲት 06 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር ቅሬታውን አጠናክሯል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ለቅሬታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ከተገቢው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ጉዳዩን በመጀመሪያ ለተመለከተው የአስተዳደር ፍርድ ቤት የማስተርስ ትምህርት ጨርሼ ስመለስ በአመልካች ምደባ የተሰጠኝ ቢሆንም በሌለ የሥራ መደብ ላይ የምደባ ደብዳቤ የተሰጠኝ በመሆኑ ሥራ መስራት ባልቻልኩበት ሥራ ላይ አልተገኘሽም በሚል ደመወዜ መታገዱ ተገቢ አይደለም የሚል ቅሬታ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ተጠሪ ምደባ አልተሰጠኝም ማለታቸው ተገቢ አይደለም፤ ምደባ ተሰጥቷቸው ሥራ ላይ ባለመገኘታቸው ደመወዛቸው መታገዱ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ከዚህ ክርክር መረዳት የሚቻለው ተጠሪ የማስተርስ ትምህርት ጨርሰው ሲመለሱ አመልካች ለተጠሪ የሥራ ምደባ ደብዳቤ እንደተሰጣቸው በግራ ቀኙ የታመነ መሆኑን ነው፡፡ ግራ ቀኙ የተካካዱበት ፍሬ ነገር ተጠሪ የተመደቡበት የሥራ መደብ በአመልካች መስሪያቤት ውስጥ በተግባር ያለ የሥራ መደብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 2/2/6 የሥራ መደብ ትርጉም እንደተመለከተው የሥራ መደብ ማለት በአንድ የመንግስት ሠራተኛ በሥራ ጊዜ እንዲሰራ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የሚሰጥ የሥራ ኃላፊነት እና ተግባር ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የስራ ምደባ ማለት ምደባውን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በሚሰጠው የመንግስት መስሪያቤት ውስጥ ሠራተኛው ባለው እውቀት፣ የሥራ ልምድ እና ክህሎት መሰረት በሥራ ሰአት እንዲያከናውን የሚሰጠው የሥራ ድርሻ ወይም ኃላፊነት ማለት ነው፡፡ ሠራተኛው እንዲሰራ በተመደበበት የሥራ መደብ ውጤታማ በሆነ መልኩ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት እንዲወጣ አሠሪው መሥሪያቤት ለሥራው ምቹ የሆነ እና የሠራተኛውን ደህንነት የሚያስጠብቅ የሥራ ቦታ እና የሥራ መሳሪያ ማቅረብ እንዳለበት፤ ተገቢውን ሥልጠና መስጠት እንዳለበት እና ሌሎች ሁኔታዎችን የማሟላት ግዴታ እንዳለበት በተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 65 ላይ ተመልክቷል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ሠራተኛውም በሥራ ሰአት በሥራ መደቡ ላይ ተገኝቶ የሚጠበቅበትን አገልግሎት የመስጠት እና ሌሎች ግዴታዎች ያሉበት መሆኑን በአዋጁ አንቀጽ 66 ላይ ተመልክቷል፡፡ ከእነዚህ የአዋጁ ድንጋጌዎች በጥቅሉ መረዳት የሚቻለው የመንግስት መስሪያቤት ለሠራተኛው ተገቢውን የሥራ መደብ እና ለሥራ መደቡ የሚያስፈልጉ አቅርቦቶችን ማሟላት እና ሠራተኛውም በስራ ሰአት በሥራ ቦታ ላይ በመገኘት ተገቢውን ሥነ-ምግባር ጠብቆ ሥራውን የማከናወን ግዴታ ያለበት መሆኑን ነው፡፡ እነዚህ ከአሠሪውም ሆነ ከሠራተኛው የሚጠበቁ ግዴታዎች ከተጣሱ ተጠያቂነትን የሚያስከትሉ መሆኑን በአዋጁ አንቀጽ 68 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ ተመልክቷል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ በአመልካች ደመወዛቸውን የማገድ የዲሲፕሊን እርምጃ የተወሰደው ተጠሪ በሥራ መደባቸው ላይ አልተገኙም በሚል ነው፡፡ ተጠሪ በሥራ መደባቸው ላይ አለመገኘታቸውን ሳይክዱ በሥራ ቦታቸው መገኘት ያልቻሉት በአመልካች የተሰጣቸው የሥራ መደብ በተግባር ባለመኖሩ መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የተጠሪ አሠሪ ሆነው አመልካች የሥራ መደብ ለተጠሪ የመሥጠት ግዴታ ያለበት ሲሆን ምደባውም በደብዳቤ ከመገለጹ በተጨማሪ በተግባር ያለ የሥራ መደብ ሊሆን እንደሚገባ ግልጽ ነው፡፡ አመልካች በደብዳቤ ተጠሪን የመደበ ቢሆንም በደብዳቤ የተገለጸውን የሥራ መደብ በተግባር በመስሪያ ቤት ውስጥ የሌለ ከሆነ አመልካች በፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 65 ላይ የተመለከተውን ሥራ እና ሥራ ቦታ አመቻችቶ የመስጠት ግዴታውን ስላልተወጣ የተጠሪን ደመወዝ ማገዱ ህጋዊ ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በደብዳቤ የተመደቡበት የሥራ መደብ በአመልካች መሥሪያ ቤት ውስጥ በተግባር አለ ወይስ የለም የሚለው የግራ ቀኙ የክርክር ጭብጥ ተደርጎ በተገቢው ማስረጃ ከተጣራ በኋላ የተጠሪ ደመወዝ መታገዱ ተገቢ ነው አይደለም ለሚለው ምላሽ የሚያገኝ በመሆኑ በመጀመሪያ ተጠሪ የተመደቡበት የሥራ መደብ በተግባር በአመልካች መስሪያቤት ውስጥ አለ ወይስ የለም? የሚለው ግራ ቀኙ በሚያቀርቡት ማስረጃ ሊጣራ ይገባ ነበር፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የአስተዳደር ፍርድ ቤት አመልካች ለሶስት አመት ተከትል ተጠሪ በሥራ ቦታ ስለመገኘት አለመገኘታቸው ተገቢውን ቁጥጥር የማድረግ ግዴታውን አልተወጣም እንዲሁም አመልካች ተጠሪ በሥራ ላይ አለመገኘታቸውን የሰአት መቆጣጠሪያ በማቅረብ አላስረዳም በሚል የተጠሪ ደመወዝ ሊታገድ አይገባም የሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰ መሆኑን የውሳኔው ይዘት ያሳያል፡፡ በእርግጥ አመልካች ለተጠሪ በሰኔ ወር 2009 ዓ.ም በደብዳቤ ምደባ ከሰጠ በኋላ ተጠሪ በተመደቡበት የሥራ መደብ ላይ እየሰሩ መቆየት አለመቆየታቸውን የመቆጣጠር ኃላፊነት እንዳለበት አከራካሪ አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ ላለፉት ሶስት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመታት ተቆጣጥሮ እርምጃ አለመውሰዱ ከሶስት አመት ተኩል በኋላ ተጠሪ በሥራ ቦታ ላይ እስካልተገኙ እና ድርጊቱ እስከቀጠለ ድረስ እርምጃ ከመውሰድ የሚያግደው ወይም እርምጃ የመውሰድ መብቱን የሚያስቀረው አይሆንም። ተጠሪ ሥራ ላይ አለመገኘታቸውን ሳይክዱ ያልተገኙበትን ምክንያት በመግለጽ የሚከራከሩ ከመሆኑ አንጻር ተጠሪ በሥራ ቦታ አለመገኘታቸውን በተመለከተ የታመነ ፍሬ ነገር ስለሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 242 መሰረት ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ የለበትም።

ሌላው አመልካች በሰበር ቅሬታው የተጠሪ የሥራ ስንብት ህጋዊ ሆኖ እያለ ደመወዝ ይከፈል መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት ያቀረበውን ቅሬታ ስንመለከት ተጠሪ ለስር አስተዳደር ፍርድ ቤት የሥራ ስንብትን በተመለከተ ያቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ የለም። አመልካችም ለተጠሪ ቅሬታ በሰጠው መልስ የተጠሪ ደመወዝ ያልተከፈለው ከሥራ በመሰናበታቸው ነው በሚል ያቀረበው ክርክር ያለም። ከስር ጅምሮ የነበረው ክርክር ከደመወዝ መታገድ ጋር ብቻ የተያያዘ በመሆኑ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ ከሥራ ስንብት ጋር ተያይዞ የተነሳው ክርክር የሚታይበት የህግ አግባብ የለም። በመሆኑም ተጠሪ አመልካችን አሰናብቻለው የሚል ከሆነ እራሱን ችሎ ክርክር የሚደረግበት በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም።

በመሆኑም የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 246 መሰረት ግራ ቀኙ በተካካዱበት ፍሬ ነገር ማለትም ተጠሪ የተመደቡበት የሥራ መደብ በተግባር በመስሪያ ቤቱ ውስጥ አለ ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ በመመስረት በግራ ቀኙ ማስረጃ በማጣራት ተገቢውን ውሳኔ ሊሰጥ ሲገባ ተገቢውን ጭብጥ ሳይመሰርት እንዲሁም ተጠሪ በሥራ ቦታ ላይ አለመገኘታቸውን ሳይክዱ አመልካች ተጠሪ በሥራ ቦታ አለመገኘታቸውን በማስረጃ አላስረዳም በሚል ምክንያት የተጠሪ ደመወዝ ሊታገድ አይገባም በሚል የደረሰበት መደምደሚያ የክርክር አመራር ግድፈት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል። ይህንን ግድፈት ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማረም ሲገባው አለማረሙ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት እና በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታረም የሚገባው በመሆኑ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል።

## <u>ውሳኔ</u>

1ኛ. የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 176/2013 በግንቦት 25 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 209017 ዓ.ም የተሰጠው ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽሯል።

2ኛ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የተዘጋውን መዝገብ አንቀሳቅሶ ተጠሪ የተመደቡበት የሥራ መደብ በአመልካች መሥሪያ ቤት ውስጥ ያለ የሥራ መደብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ከግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ጋር አገናዝቦ በመመርመር ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1 መሰረት ተመልሶለታል።

3ኛ. በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

**ትእዛዝ**

በዚህ መዝገብ በታህሳስ 22 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም